# አካኪ ዘራፍ !!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

ዘራፍ ! ዘራፍ !
እኔ ጎበዙ፤
ያይጥ እርጉዙ፤
በምላስ ካራ፤
የማስፈራራ፤
በሰድብ ዱላ የማንጠራራ፤
ዜጎች ሲቆሉ በራብ በችግር፤
አገር ለባዳ የምቸረችር፤
በዘር በጎሳ የምከፋፍል፤
የምገነጥል የማስገነጥል፤
ዘራፍ ! ዘራፍ !

ተከዜ ልብሴ፤
ዓባይ ፈረሴ፤
ዘራፍ ! መጣሁ !
ዓባይ ፈረሴን ተፈናጥጬ፤
ግብፅን ላጠጣት ባሩድ በጥብጬ፤
መጣሁ ! መጣሁ !
ተፈጥሮን ሳርቅ መንገድ ላስቀይር
ዓባይ እንዲፈስ ከናስር ክትር፤
ወደ ጣና ሃይቅ ወደ ባሕር ዳር፤
መጣሁ ! መጣሁ !
ዘራፍ ! ዘራፍ !

ኅዳር 16 2003 ዓ.ም. (Nov. 25/11/2010)

መካሪ ላጡት ለአቶ መለስ ዘናዊ፤

ኢትዮጵያ መች ጠላት አጣችና: ሌላ ጠላት ይጋብዙልናል ? ሱማሌ ገብተው የጫሩት እሳት: እስከዛሬ እየጨሰ መሆኑን ዘነጉት ?
በግብፅ ሰበብ ሃይማኖት አክራሪ የሆኑ የአረብ አገሮች በሙሉ በኢትዮጵያ ላይ እንዲነሱና የሃይማኖት ጦርነት (ጂሃድ) እንዲያውጁ የሚጋብዙልን ?

ኧረ ጎበዝ እኝህን ሰው ምነው ሃይ የሚል ሰው ጠፋ?!

የዓባይ ጉዳይ የሚፈታው በብልሃት፤ በማስተዋልና በጥበብ፤ ሰከን ባለ መልኩ ፤ በዓባይ ጉዳይ ላይ ጥናት ካደረጉ ምሑራን ጋር ምክክርና ሰሴት አድርጎ እንጂ በአካኪ ዘራፍ አይደለም።

ደግሞስ እርስዎ አይደሉም እንዴ ለግብፆች በዓባይ ወንዝ አካባቢ በሬት እየቸረቸሩላቸው

ያሉት? ታዲያ ያሁኑ አካኪ ዘራፍ ምን ለመቧጠጥ ነው??